**Solidarity Committee for Ethiopian Political Prisoners (SOCEPP-Canada)**
የኢትዮጵያ ፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ በካናዳ (ኢፖእአኮ-ካናዳ)
**Email:** socepp.can@humanrightsethiopia.com **and** socepp.can@sympatico.ca
Web: www.humanrightsethiopia.com

---

የካቲት 14፣ 2011 ( ፌበርዋሪ 21፣ 2019)
ለተከበሩት አቶ ብርሃኑ ጸጋዬ
የፌደራል ጠቅላይ ቃቢህግ
አዲስ አባባ

የተከበሩት አቶ ብርሀኑ

ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አህመድ በህዳር 3፣ 2011 የአባራሽ በርታንና የሌሎችንም መዳረሻቸው ያልታወቀ የፖለቲካ እስረኞች ሁኔታ በጉጉት ለሚጠብቁት ወዳጅና ዘመዶቻቸው እንዲሁም ለሙብት ተሟጋቹ ማህበረሰብ እንደያሰታውቁን በመጠየቅ ደብዳቤ መጻፋችንን ተከትሎ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአማርኛው ፕሮግራም እርሰወን በኖቨምበር 15፣ 2018 እንዳነጋገረ ይታወሳል። በዚያም ቃለ ምልልስ ውስጥ የወይዘሮ አበራሽ በርታን ፣ለማ ሃይሌ፣, ሙሉ አምባውን፣ ፀጋየ ገብረመድህንን፣ ይስሀቅ ድበረጽዩንን፣ በለጠ አምሃ, ሐጎስ በዛብህ , ስጦታው ሁሴን, ተከላይ ገ/ሥላሴ,, አባይነህ ሽፈራው , አበበ ዓይነኩሉ ፣አዛናው ደምል , ደምሴ ተሰፋዬ ወዘተ ጉዳይ እስከቃለምልልሱ እለት እንደማያውቁ ገልጸው ሁኔታውን እንደሚከታተሉ እጅግ ትልቅ ተስፋ ሰጭ የሆነ ምላሽ እንደሰጡ ይታወሳል።

*https://www.facebook.com/ethiopianbrief.ethio/videos/1375079972626519/UzpfSTEwMDAxMzgzMjI4Mjc3Mzo1NDQ0NDQzNTkzNTk5Njk/*

ያንን ቃለምልልስ ተከትሎም የወይዘሮ አበራሽ በርታ፣ አቶ ሙሉ አምባውና የሌሎችም መዳረሻቸው አልታወቀው የፖለቲካ እስረኖች ወዳጅኛ ዘመዶች የእስረኞቹን ሁኔታ በተመለከተ ምን አዲስ ጉዳይ እንዳለ ለማወቅ እጅግ በጉጉት እየጠበቁ ይገኛሉ።

ከነዚህ በጉጉት ከሚጠብቁ ኢትዩጵያውያን ውስጥ ብዙወች እኛን በተደጋጋሚ በስልክ በኢሜል እንዲሁም በግንባር በማግኘት ምን አዲስ ነገር እንዳለ በተደጋጋሚ ይጠይቁናል። ከ 20 አመት በላይ መዳረሻቸውን ያላወቋቸውን የወዳጅ ዘመዶቻቸውን መዳረሻ ለመወቅ የቤተሰቦቻቸውንም ሆነ የ እኛን ድርጅት ጉጉት ከቡርነትወም ሆነ መንግስት በትክክል እንደሚገነዘቡ እርግጠኞች ነን።

የዛሬው ደብዳቤያችን ዋና አላማም ፣ በገቡት ቃል መሰረት የተካሄደ ወይንም የተጀመረ ማጣራት ካላ እንዲገልጡልን በአክብሮት ለመጠየቅ ነው። የተጀመረ ጉዳይ ከሌለም ባስቸኳይ እንዲጀመር ለመማፐን ነው።

እርስወም እንደሚያውቁት የዘገየ ፍትህ  እንደተከለከለ ፍትህ ሊመሰል ይችላልን አሁንም ለዚህ ጉዳይ ልዩ አጽንኦት በመስጠት እልባት እንዲያገኝ እንደሚያደርጉ ባለሙሉ ተስፈ ነን።

በእኛ  በኩል ምርመራውን ሊያግዝ በሚችል መንገድ ሁኑ ለመተባባር ምን ጊዜም ዝግጁ መሆናችንን ስንገልጽ በታላቅ ትህትና ነው።

ከታላቅ አክብሮት ጋር

አከሊሉ ወንድአፈረው
የ ኢትዮጵያ ፖለቲካ አስረኞች አንድነት ኮሚቴ ካናዳ
ሊቀመንበር
ግልባጭ፣ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት፣ ለፕሬዚደንት ጽህፈት ቤት